DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ነሀሴ (August) 8, 2016

ውድ የዲሲፒኤስ ተማሪዎች ወላጆች፣

ለ 2016-2017 የትምህርት ዓመት እንኳን በሠላም አደረሰዎት! ለመጀመሪያ ጊዜ ልጆቻችሁን በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ለማስገባት ወደዚህ ለምትመጡና ወደ ዲሲፒኤስም ለምትመለሱ ወላጆች፣ ዲሲፒኤስን ለልጆቻችሁ በመምረጣችሁ አክብሮት ይሰማናል።

በዚህ ዓመት፣ የእርስዎን ትምህርት ቤት ጨምሮ 11 የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች እንደተራዘም የትምህርት ዓመት ቅጥር ግቢ ቀደም ብለው ከወዲሁ ተከፍተዋል። ቤተሰቦቻችን ከትምህርት ቤቶች ስለሚፈልጓቸው ነገሮች የሚሉትን ሰምተን፣ ለተማሪዎች ይህንን እድል ለመፍጠር ከትምህርት ባለሙያዎቻችን ጋር አበረን ሠርተናል።

የበለጠ የትምህርት መገብያ ጊዜ ለልጅዎ ታላቅ ውጤት ያስገኛል። በየዓመቱ መገባደጃ ላይ፣ ልጅዎ እንደ ዓለም ቋንቋዎች፣ ጥበብ እና ሙዚቃ፣ ንባብ እና የሂሳብ ትምህርት፣ የሣይንስ ቤተሙከራ፣ እና አካላዊ እንቅስቃሴ ለመሳሰሉት ነገሮች ተጨማሪ የትምህርት ወር ያገኛል። በተራዘመ የትምህርት ዓመት፣ ከመዋዕለ ሕጻናት እስከ 8ተኛ ክፍል ድረስ የሚማር ተማሪ፣ በጠቅላላ የ 18 ወራት ተጨማሪ የትምህርት ጊዜ የሚያገኝ ሲሆን፣ - ይህም ባጠቃላይ ሙሉ የሁለት ዓመት የትምህርት እድገት ተገናጸፈ ማለት ነው።

ከተራዘም የትምህርት ዓመት ፕሮግራማችን በተጨማሪ በዚህ ዓመት በዲሲፒኤስ ወደፊት የሚያዩዋቸው ጥቂት ነገሮች ከዚህ በታች ቀርበዋል፤

- **አዳስ ትምህርት ቤቶች፤** ይህ ቀጥታ የ 5ተኛ ዓመት የተማሪዎች ምዝገባ እድገታችን ሲሆን፣ ፍልጎቶችን ለማሟላት አዲስ ትምህርት ቤቶች እየከፈትን ነው። ሮን ብራውን (Ron Brown College) ለኮሌጅ ትምህርት ዝግጅት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በዋሽንግተን ዲሲ የመጀመሪያው የወንዶች የሕዝብ ትምህርት ቤት ብቻ ሲሆን፣ በአመራር ላይ ትኩረት ያደረገ የዲስትሪክቱ ወጣት ወንዶች ተማሪዎቻችንን የሚያሰለጥን ነው። ማክፋርላንድ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (MacFarland Middle School) በዚህ መጸው ወራት በእን ጊሊዘኛ እና በስፓኒሽ ቋንቋዎች ላይ የተመረኮዙ ኮርሶችን የሚያስተምር እንደመንታ ትምህርት ቤት ሆኖ ይከፈታል።
- **ነው ኮርነርስቶንስ (New Cornerstones):** በበጋው ወቅት፣ ኮርነርስቶን ጊዜውን ተከትሎ እንዲሄድ እና እንዲስፋፋ ለማድረግ፣ የዲሲፒኤስ መምህራን የሠሩ ሲሆን፣ ይህም ከቅድመ መዋዕለ ሕጻናት እስከ 12ተኛ ክፍሎች ድረስ የሚገቡ ተማሪዎች፣ እያንዳንዳቸው የሚያጓጉ ትምህርቶች እና ፕሮጀክቶች፣ ብስክሌት ከመጋለብ እና ባትሪ ከመሥራት አንሥቶ እስከ ተክሎችን እርስ በእርስ እስከማዳቀል እና ሙዚቃ እስከማቀናበር ትምህርት ድረስ ዕውቀት የገበዩት ነው። በዚህ ዐይነት ልጆችዎ የቀሰሙትን ዕውቀት፣ በሚያጓጓ በዕውን ዓለም ይዘቶች ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሏቸው ይሆናል።
- **አዲስ ሥርዓተ ትምህርት፤** በዚህ መጸው ወራት ዲሲፒኤስ፣ ከመዋዕለ ሕጻናት እስከ አልጀብራ ሁለት (Algebra II) ለሚማሩ ተማሪዎች የዩሪካ ሂሳብ ሥርዓተ ትምህርት (Eureka math curriculum) ይዘረጋል። ዩሪካ (Eureka) ልጅዎ ችግሮችን የመፍታት ክህሎቶች እና በሂሳብ ቀልጣፋ ችሎታ እንዲኖረው መርዳት የሚያስችል የጋራ የሪሶርሰ ቅንጅት ማለትም Common Core -aligned የትምህርት ሪሶርሶችን ሁሉ የሚያካትት ነው።

እንደ እርስዎ እኔም፣ ልጆቻችን ትልቅ ደረጃ ላይ ለመድረስ ባላቸው አቅም የምተማመን ኩሩ የዲሲፒኤስ ተማሪ ወላጅ ነኝ። ግባችን፣ ልጅዎ ሕልሙን እንዲጨብጥ ወይንም ሕልሟን እንድትጨብጥ ለመረዳት እንዲቻል በዚህ ዓመት ከእርስዎ ጋር አብሮ ለመሥራት ነው። በትምህርት ቤትዎ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የማበረታታዎት ሲሆን፣ በሶሻል ሚዲያ ላይ (@dcpublicschools on Facebook, Twitter, እና Instagram) እንዲከታተሉን እና እንዴትም እየሠራን እንደሆነ እንድናውቀው ያድርጉን።

አዲሱ የትምህርት ዓመት ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ግሩም ትምህርት መጀመሪያ ዓመት እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ። እኛ ዲሲፒኤሶች ስንሆን ይህንንም ተግባራዊ እናደርገዋለን!

ከአድናቆት ጋር።

Kaya Henderson
ቻንስለር፣ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Chancellor, DC Public Schools)